# ★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

**ዴሞ ቅጽ** 34 **ቁጥር** 1 **መስከረም** 2001 **ዓ.ም.**


## ተደራጅቶ መታገል፥ ትግሉ ማሸነፍ

*ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ ቤታቸውን አጽድተው በግ ወይም ዶሮ አርደው፥ ጠላ ወይም ጠጅ ጠምቀው፥ ከጎረቤት ወይም ከዘመድና አዝማድ ጋር አዲሱን ዓመት በድግስ በዘፈንና በዜማ የመቀበል ልማድና ባህል የነበራቸው ኢትዮጵያውያን በተለይም የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች በምግብ እቃዎች እጥረትና በዋጋቸው ንረት ዘንድሮ በዓሉን በጭንቀትና በሀዘን አሳልፈውታል:: ረመዳንን እየጾሙ ያሉ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ወገኖቻችንም የምግቡ ዋጋ ንረት በጾም የደከመ ሰውነታቸውን ለመጠገን ሰቀቀን እየሆነባቸው መሆኑ የሚታይ ነው:: ወትሮም ቢሆን በትርፍራፊ ሆዱን ሞልቶ የሚያድረው በረንዳ አዳሪ ደግሞ የዋጋ ንረቱ ያችውን ትርፍራፊውን ቀንሶበት ከአንድም ሁለት ቀን አለምግብ በረሃብ ጊዜውን ማሳለፍን ተለማምዶታል:: ሁሉም የወያኔን በደል እያወገዘ ምን ይመጣ ይሆን? የሚል የጭንቀት ባህር ውስጥ እየዋኘ ያለበት አሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ ነው ያለው::*

*ላለፉት* 18 *ዓመታት በጠመንጃ ኃይል ሥልጣን ይዞ የሕዝብ መብቶችን አፍኖ ፥ የመጨቆኛና የማፈኛ ተቋሞችን አጠናክሮ ሕዝቡንም አገሪቱንም በመበዝበዝ በመጨቆን ላይ የሚገኘው ጠባቡ የወያኔ ቡድን አሁንም ከምን ጊዜውም በላይ በእብሪት ተወጥሮ፥ አገዛዙን አጠናክሮ በሥልጣን ላይ ተደላድሎ ይገኛል:: ባለፉት* 18 *የመከራ ዘመናት በበዙ መቶ ሺ የሚቆጠሩ ሕጻናት አለ አባትና አለእናት፥ ወንድም አለ እህት፥ እህት አለ ወንድም፥ ወላጆች አለ ልጅ፥ አዛውንቶች አለ ጧሪ ቀባሪ፥ ፍቅረኞች አለ ወዳጅ፥ ቀርተዋል:: በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ወገኖች፥ ከመንገድ ላይ፥ ከቤታቸው፥ ከሥራ ቦታቸው እየታፈኑ፥ በገፍ እየታፈሱ፥ በጉድጓድ እስር ቤቶች፥ በበረሃ ማጎሪያ ጣቢያዎች፥ በተለያዩ እስር ቤቶች እንደትቢያ ተጥለው ወድቀዋል፥ መዳረሻቸው ጠፍቷል፥ አሰቃቂና ኢሰብአዊ በሆነ ሁኔታ ሰውነታቸው ተቀጥቀጧል፥ ተመትሯል:: በረሃብ ተጠብሰዋል፥ በበሽታ ማቅቀዋል:: ለተወሰኑ ወቅቶች የነበሩ የይስሙላ ማስመሰያ መብቶች እስከናካቴው ተገድበዋል፥ በተወሰነ ደረጃ በነፃነት ይንቀሳቀሱ የነበሩ የፕሬስ ተቋሞች፥ የሙያ ማሕበራት የፖለቲካ ድርጅቶች ወዘተ...ፈርሰዋል:: አምባገነንነት ዛሬ ከምንጊዜውም በላይ ነግሶና ገንኖ ይገኛል::*

*አገራችን በዓለም ከሚገኙ የመጨረሻ* 10 *ደኃ አገሮች ውስጥ አንዷ ሆና ሳለ ፥* 80 *ከመቶ የሚሆነው ሕዝባችን በቀን ከሁለት የአሜሪካን ብር በታች ገቢ የሚያገኝ ሆኖ ሳለ፥ ሥራ ሊሠራ ከሚችለው የሕብረተ ሰብ ክፍል መካከል* 70 *ከመቶ የሚሆነው ሥራ አጥ ሆኖ እያለ የሕዝባችን ኑሮ እንደተሻሻለና አገሪቱም በኢኮኖሚ እያደገች የሄደች መሆኗን በየቀኑ*

በየደቂቃው ይደሰኮራል። አንድ ኩንታል ጤፍ ከ1000 ብር በላይ፥ አንድ ዶሮ ከሰማንያ ብር በላይ እየተሸጠ፥ ረሃብ በለምነቱና በአምራችነቱ በታወቀው በደቡብ ኢትዮጵያ ሳይቀር ገብቶ ዜጎችን፥ ሕጻናትን እያሰቃየና የሞት አፋፍ ላይ እያደረሰ ባጠቃላይም ከ10 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን እንደሚራቡ ተነግሮ እንደተለመደው ምጽዋት ከዓለም ቸር አገሮች እየተጠየቀ ባለበት ሁኔታ ከጥቅማቸው በስተቀር ሌላ የማይታያቸው የወያኔ ሹማምንትና ጋሻ ጃግሬዎቻቸው "ረሃብ የለም ልማትም እየተስፋፋ ነው መንግሥት አገሪቱን ከድህነት አላቆ፥ በእድገት ባቡር ላይ አስቀምጦ እንድትገሰግስ እያደረጋት ነው" ወዘተ... የሚሉ አደንቋሪ የሆኑ ልፍለፋቸውን በየአደባባዩ ሲያስደምጡን አይናቸውን በጨው እያጠቡ ነው:: የቻይና ኢኮኖሚ በአንድ ፓርቲ ቁጥጥር ስር አድጓልና እንደቻይና ለእድገት ለሰላምና ለመረጋጋት አንድ ፓርቲ ያስፈልገናል የሚለውን መፈክር ውስጥ ውስጡን እያቅራሩ ራሳቸውን ለዚሁ አጭተው ሁኔታዎችን እያመቻቹ መሆኑንም እያየን ነው:: በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ የወያኔ ቡድን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በቀጥታ የሚያደርሰው በደል ሳያንሰው ከጥቂት ዓመታት በፊት ከአጋሩ ከሻዕቢያ ጋር ባደረገው ጦርነት በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ወጎኖቻችንን ሕይወት በጦር ሚዳ ላይ እንዳወደመውና ቀሪዎችንም አካለ ስንኩላን እንዳደረጋቸው ሁሉ አሁንም የባዕዳንን ፍላጎት ለማሟላትና በምትኩም ድጋፋቸውንና ትብብራቸውን ለማግኘት ሲል ወታደሮችን ወደ ሶማሊያ ልኮ የወገኖቻችን ደም በከንቱ እንዲፈስ የሀገሪቷም አንጡራ ሀብት እንዲባክን እያደረገ ነው:: ይህ ጣልቃ ገብነት አገራችንን በሌሎች በተለይም በእስልምና ተከታይ ሀገሮች በጠላትነት እንድትታይ ያደረጋት ከመሆኑም በላይ ለከባድ ጥቃትና ጦርነት ያጋለጣት መሆኑ ግልጽ ነው::

ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎች ዋጋ መናር፥ የሥራ አጡ ብዛት፥ የተላላፊ በሽታዎች መዛመትና መስፋፋት፥ የረሀቡና ችግር መስፋፋት፥ የመብቶች መረገጥ፥ የበደሎች መስፋፋትና መጠናከር፥ የሀገራችን ሉዓላዊነትና አንድነት አሳሳቢና አስጊ ደረጃ ላይ መድረስና ሌሎችም ተዘርዝረው የማይልቁ ምስቅልል በደሎች ሕዝባችንን አስመርረውታል፣ አስቆጥተውታል፥ ለለውጥ ቁርጠኛ አቋም እንዲወስድ አድርገውታል::

በደልን በእምቢተኛነት ለመመከት፥ አምባገነኑን አስከፊ አገዛዝ በአመፅ ለመደምሰስ ሕዝብ ቁርጠኛነቱን እያሳየ ባለበት ወቅት፥ የትግል ሃሞቱን ለመግደል፥ ትግሉን ወደ ኋላ ለመጎተት የተለያዩ ሴራዎች እየተሸረቡ መሆናቸው በገሃድ የሚታይ ነው:: ባንድ በኩል የጨቋኙን ቡድን ጊዜያዊ ጥንካሬ በሌላ በኩል የተቃዋሚ ኃይሎችን ድክመት እንዲሁም የሕዝብን ዝምታና ትእግስት መሠረት በማድረግ ከእንግዲህ ወያኔ ብዙ ዓመት ይገዛል የሕዝብ ትግል አብቅቷል፣ የወያኔን ኃይል የሚቋቋም ምንም ኃይል የለም፥ አምላክ አንድ ሁኔታ ካልፈጠረ የኢትዮጵያ ጉዳይ አልቆለታል ፥ ስለሆነም ጥሩ ቀን እስኪመጣ ድረስ ዝም ብሎ የሚመጣውን ሁሉ መቀበል ነው የሚሉ ተስፋ አሳጪና ጨለምተኛ አመለካከቶችን የሚያስፋፉና የሚያሰራጩ ክፍሎች ተከስተዋል:: ይህን አመለካካት ከሚያስፋፉትና ከሚያሰራጩት መካከል ሁኔታዎችን በሚገባ ለመረዳት የተሳናቸው የዋህ ወገኖች የሚኙበት መሆኑ አከራካሪ ባይሆንም በአብዛኛው ግን የወያኔ አባሎችና ጋሻ ጃግሬዎች እንዲሁም የራሳቸው ጥቅም ከሀገር ጥቅም የበለጠባቸው ሆዳሞች ና ሀሳዊ መሲሆች ናቸው::

የኢትዮጵያ ሕዝብ በትረ መንግሥቱን በመያዝ በላዩ ላይ ተኮፍሰው፣ መብቱን ገድበው ሲረግጡትና ሲመዘብሩት በቆዩት ላይ፥ ከጭቆናና ከበደል ለመላቀቅ፥ የዕድሉና የመብቱ ባለቤት ለመሆን ለበርካታ ጊዜያት ቆራጥ ትግል አካሄዷል፥ ከገዥዎች ጋር ግብግብ ገጥሟል፥ የሕይወት፥ የአካልና የ ብረት መሥዋዕትነት ገብሯል:: እንደ እድል ሆኖ በሚገባ ባለመደራጀቱ ወይም የነበሩት ድርጅቶች ባለ መጠናከራቸው በተጋድሎና በመሥዋዕትነት ያገኘውን ድል በሌላ ቀማኛ ቢቀማም፥ ድሉን ቀምተው ሥልጣን ላይ በተኮፈሱት ቡድኖች በተደጋጋሚ ለባሰ መከራና ችግር ቢዳረግም ግምባሩን ያጠፈበት፥ አንገቱን ያጎነበሰበት፥ ትግሉን ያቋረጠበት ጊዜ የለም:: የኢትዮጵያ ሕዝብ በአፄው መንግሥት ላይ ለዘመናት ያካሄደው ትግል በየካቲት 66 ጎምርቶ ለድል በቅቷል:: የድሉን ፍሬ ራሱን ወታደራዊ

ደርግ ብሎ የጠራው ጠራቢ ቡድን ሞጭልፎ ወስዶና ለ17 ዓመት ያህል በሥልጣን ተኮፍሶ እንደስጋ እየመተረ÷ እንደ ብረት እየቀጠቀጠ÷ እንደሰም እያቀለጠ ሲገዛው ሕዝቡ ትግሉን ለአፍታም ያህል ያቋረጠበት ጊዜ የለም:: የሕዝብን ብሶትና ቁጭት መሠረት አድርጎ÷ የሕዝብ እምቢተኛነትንና አይበገሬነትን መከታ አድርጎ÷ የሕዝብን ትግል የሕዝብን ትብብር ተላብሶ÷ በሕዝብ እርዳታ ደርግን ለመጣል የበቃው የወያኔ ቡድን በጠመንጃ ኃይል ሥልጣን በቁጥጥሩ ስር ካስገባ ጀምሮ የሕዝብ ቁጣ÷ የሕዝብ ትግል÷ ሳያውተረትረው በሰላም ያለፈበት ጊዜ ካለ በቁጥር አነስተኛ ነው:: የወያኔ ቡድን ገና በአፄው ቤተ መንግሥት ሲገባ የደረሰበት ተቃውሞና ያካሄደው ፍጅት፤ በተለየዩ ጊዜያት ተማሪዎች ፤ ወጣቶች÷ ነጋዴዎች÷ መምህራን÷ ሠራተኞች÷ ገበሬዎች ወዘተ... ያካሄዱት እልህ አስጨራሽ ትግል፤ በአዲስ አበባ አንዋር መስጊድ÷ በጎንደር አደባባይ እየሱስ÷ የተደረጉት የሕዝብ ተቃውሞዎች፤ በአረካ÷ በአዋሳ÷ በጋምቤላ÷ በድሬዳዋ÷ በመቀሌ ወዘተ...የተደረጉት ትግሎች፤ አሁን እንኳ በቅርቡ በ97 ምርጫ ወቅትና በኋላ የታየው የሕዝቡ እምቢተኛነትና ትግል እንዲሁም የተከተለው እልቂት፤ በሕይወታቸው በአካላቸው በንብረታቸው መሥዋዕትነት የከፈሉት ዜጎች እና ሌሎችም የሚያረጋግጡት ነገር ቢኖር የወያኔ አገዛዝ የሕዝብ ተቃውሞና ትግል ሳያጋጥመው በሰላም ያለፈ አለመሆኑን ነው:: ስለሆነም ሕዝብ ሲታገል ቆይቷል÷ አሁንም እየታገለ ነው:: ወደፊትም ይታገላል::

በሕዝብ ትግል ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ለመቸለስ ሕዝብን ከትግል ለማራቅና ባንጻሩ የወያኔ አገዛዝ ያለ ተቃውሞ ተደላድሎና ተመቻችቶ እንዲቀጥል ለማድረግ እየተሸረበ ያለው ሌላው ተንኮል ደግሞ የሕዝቡ የትግል መሣሪያ የሆነውን ድርጅትን በማንኳሰስ÷ የተደራጁትን ለማፍረስና ለማዳከም÷ ሕዝብም ከመደራጀትና ከመታገል እንዲርቅ ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ቅስቀሳዎች በማስፋፋት በሕዝቡ ውስጥ ውዥንብር ለመፍጠር እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ ነው:: ከድርጅት አገር ይቅደም የሚል በማር የተቀባ መፈክር እያስተጋቡ÷ በተጨባጭ ግን ተደራጅተው የሚታገሉት ድርጅቶች ፈርሰው ይሰባበሩ እያሉ የሚያላዝኑ ክፍሎች ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል:: በቁርጠኛነት እየታገሉ ባሉ ድርጅቶች ላይም አስፀያፊ ዘመቻ እያስፋፉ በእርስ በርስ እንካሰላንቲያ የትግሉ ጊዜ እንዲራዘም እያደረጉ ነው:: በወቅቱ የሚታየውን የፖለቲካ ድርጅቶች ችግር እያጎሉ፤ እስካናካቴው በፖለቲካ መደራጀት ምን ይጠቅማል? ዋናው በድርጅት መልክ ሳይደራጁ እንቅስቃሴ በመፍጠር ሀገርን ነፃ ማውጣት ነው የሚል ትጥቅ አስፈቺና ትግል አስጣይ ቅስቀሳዎች ከዚያም ከዚህም የሚያስተጋቡ አወናባጆች በፖለቲካው መድረክ የበላይነትን ለማግኘት እየጣሩ ነው:: ይህን ከሚያስተጋቡት መካከል ነገሩ ያልገባቸው የዋሆች መኖራቸው ግልጽ ቢሆንም በዋና መልኩ እየተሰራጨ ያለው ግን በወያኔ አባላትና በአጫፋሪዎቻቸው መሆኑ ክርክር የሚያስገባ ጉዳይ አይደለም:: ሕዝብ የመሪ ድርጅት ያለህ እያለ ፈጣሪውን በሚማፀንበት በአሁኑ ወቅት የተደራጁት ድርጅቶች ፈርሰው እንዲበታተኑ መታገል በቀጥታ ወያኔ እስከወዲያኛው በሥልጣን ላይ እንዲቆይ መርዳትና መተባበር እንጂ ሌላ ትርጉም ሊኖረው አይችልም:: በፖለቲካ ድርጅቶች በኩል በዓላማም ሆነ በአሠራር÷ በአደረጃጀትም ሆነ ተዐማኒነትን በማትረፍ በኩል ችግሮች መኖራቸው ግልጽ ነው:: ከዓላማ ጥራት ችግር ሆነ ከስልት መጉደል÷ ሁኔታዎችን በሚገባ ካለመረዳት ሆነ የሩቁን ለማየትና የወደፊቱን ለመተንበይ ካለመቻል በፖለቲካ ድርጅቶች በኩል የተደረጉ ስህተቶች በርካታ ናቸው:: የሕዝብን ፍላጎት ያላሟሉ÷ ያልሆነ ተስፋ ሰጥተው ሕዝብን ለመሠዋዕትነት የዳረጉ÷ ተስፋ ያስቆረጡ ድርጅቶች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም:: ይህም ሳያንስ ወያኔ በስውር ያንቀሳቀሳቸው፤ ሕዝባዊ መልክ ይዘው ለሕዝብ የቆሙ መስለው÷ ሕዝብን እናደራጃለን÷ እናታግላለን በማለት ወዲያ ወዲህ ሲራወጡ የነበሩ በመጨረሻም ሕዝቡን የካዱና ለባሰ መከራ የዳረጉ ከሃዲዎችም በድርጅት መልክ በመንቀሳቀስ ሕዝብን ሲያታልሉ መክረማቸውን አይተናል:: ይህ ሁሉ ችግር መኖሩ ግን የድርጅትን አስፈላጊነት አይደመስስም:: የሕዝብ ትግል አቸናፊነት አጠራጣሪ ባይሆንም በድርጅት ያልተመራ÷ በድርጅት ያልተዋቀረ የሕዝብ ትግል ግቡን ሊመታ አይችልም÷ ሳይጠናከር በእንጭጩ ይመታል÷ ይደመሰሳል:: በ97 ምርጫ ወቅት ሕዝብ ድምፁን ለማስመለስ ያደረገው ተጋድሎና የከፈለው መሠዋዕትነት በተገቢው ደረጃ ባለመዳራጀቱ ግቡን ሳይመታ ቀርቷል::

ግለሰቦች በተለይ በሀገራዊ ጉዳዮች የተለያዩ አመለካከቶችና እምነቶች ሊኖራቸው ይችላል። ድርጅት የግለሰቦች ስብስብ እንደመሆኑ መጠን እንደግለሰቦቹ እምነትና አመለካከት ሊለያዩ ይችላሉ ። በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የተለያዩ ድርጅቶች መኖራቸው፥ የሚጠበቅ ነው። በዓለም ላይ የሚታየውም ክስተት ይኸው ነው። አንድ ወጥ ድርጅት ሊኖር የሚችለው በአምባገነኖች ሥርዓት ብቻ ነው። የሕዝቡን ትግል አስተባብሮ አምባገነኑን ቡድን ከሥልጣን ለማስወገድና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን እውን ለማድረግ የድርጅቶች መተባበር አስፈላጊ መሆኑ አከራካሪ አይደለም። እነዚህ ድርጅቶች በተለያዩ ምክንያቶች መተባበር ካቃጣቸው ሁሉም ተሰባብረው ይጥፉ ማለትና ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ ወዲያና ወዲህ ማለት ሕዝብ ድርጅት አልባ ይሁን፥ የሕዝብ ትግል ያቁም ያብቃለት፥ እኛም ዝም ብለን እየተገዛ እንኑር እንደማለት ይቆጠራል። ከአሸባሪ አምባገነን ቡድን የስቃይ የጭቆናና የብዝበዛ አገዛዝ ሕዝባችንን እና አገራችንን ለማላቀቅ ተደራጅቶ መታገል፥ ታግሎ ለሀገርና ለወገን መሥዋዕትነት መክፈል ወሳኝ ነው። በአምባገነንነት ዘመን ተደራጅቶ መታገል ታግሎም መስዋእትነት መክፈል የዜግነት ድርሻና ግዴታ እንጂ የግል ጥቅም ማፍሪያና ማራመጃ ሊሆን አይችልም። አይሆንምም።

ተደራጅቶ መታገል አጠያያቂ ባልሆነበት ባሁኑ ወቅት ዐቢይና መልስ የሚሻው ጥያቄ እንዴት? በምን ስልት? ታግለን ይህን አውሬ ቡድን ከሥልጣን እናስወግድ የሚል ነው። ለድል የሚያበቃ ትግል ስልቱ ምን መሆን አለበት? አደረጃጀቱስ ምን መልክ ይኑረው ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት፥ ያለፍንበትን ሁሉ በዓይነ ህሊናችን ቃኝተን፥ ስሜታዊ ባልሆኑና እውነታን መሠረት ባደረጉ ትንተናዎች ላይ ተመክሮአችንን ገምግመን፥ አቋማችንን መርምረን፥ ጥንካሬያችንን አረጋግጠን፥ ስህተታችንና ድክመታችንን አርመንና አስተካክለን ለመሄድ የመንፈስ ቁርጠኛነትን መላበስ ያስፈልገናል። ከተመክሯችን በመጀመሪያ መረጋገጥ ያለበት ሐቅ ቢኖር ኢሕአፓ በተደጋጋሚ በልሳኖቹ ሲገልጽ እንደቆየው በሥልጣን ላይ ያለው ቡድን ከተደራጀ ሕዝባዊ ትግል ውጭ ሥልጣን ለሕዝብ ለማስረከብ ፍላጎትም እምነትም የሌለው መሆኑን ነው። ቀደም ሲል በታጋይ ኃይሎች ውስጥ ውዥንብር ለመፍጠር ከፍተኛ ሚና የተጫወቱት የወያኔ አስመሳይና የተንኮል ሴራዎች -የቀልድ ነፃነቶች፥ የቧልት ምርጫዎች ወዘተ...- በተለይ በግንቦት 97 ምርጫ እርቃናቸውን ወጥተዋል። ከእንግዲህ ወያኔ በሚያካሂዳቸው የማስመሰያ እንቅስቃሴዎች የሚታለል የሕዝብ ወገን የለም። በምህላና በልመና ወይም በይስሙላ ምርጫዎች ወያኔ ሥልጣን ለሕዝብ ያስረክባል ተብሎም የሚጠበቅ አይደለም። ይህን ለማለት የሚደፍሩ ካሉ የወያኔ አባላትና ጋሻ ጃግሬዎች ወይም የጥቅም ተጋሪዎች ብቻ ናቸው። ስለሆነም ወያኔ ከሥልጣን ሊወገድ የሚችለው በተደራጀ ሕዝባዊ ትግል ብቻ ነው የሚለው ዐቢይ ሀሳብ መጨበጥ ይኖርበታል።

ባለፉት ዓመታት በታጋዩ መካከል የልዩነት ነጥብ እንዲሆን ተደርጎ ውዥንብር ፈጥሮ የነበረውም የትግል ስልት ጥያቄ ባሁኑ ወቅት ግልጽነት ሊይዝ ይገባል። ሕጋዊ ሆኖ ድምፅ በማሰማት መሠረታዊ ለውጥ ማምጣት ይቻላል የሚል እምነት ኢሕአፓ ኖሮትም አያውቅ አሁንም የለውም። ስለሆነም የፓርላማ አባል ሆኖ ተቃውሞ ማሰማት ወይም ወያኔ በሚፈቅደው የዜና ማሰራጫዎች ላይ በአገዛዙ ላይ ነቀፌታ ማሰማት ወያኔን የሕዝብን መብት እንዲያከብር ያደርጋል፥ ሀገራችንንም ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ያዘጋጃታል ብለን አናምንም። በዚህ መልክ የሚደረጉት ተቃውሞዎች ለሕዝባዊ ትግሉ አጋዥ ሊሆኑ ይችላሉ የሚል አመለካከት ቢኖር እንኳን ብቻቸውን ለውጥ ማምጣት የማይችሉ መሆናቸው ግልጽ ሊሆን ይገባል።

ከዚህ ውጭ ግን የትግል ስልት ጥያቄ አከራካሪ ሊሆን አይገባም። ተደራጅተው ትግሉን የሚመሩ ኃይሎች የሰላማዊ አመፅንም ሆነ የትጥቅ ትግሉን አመችነትና ውጤታማነት እየገመገሙ አንዱን ሆነ ሁለቱን በማደጋገፍ ወደ ተግባር በመለወጥ ትግሉን ማፋፋም ኃላፊነትና ግዴታቸው ነው። በህቡዕ የተደራጁ፥ በሚገባ የተመሩና የተቀነባበሩ ሰላማዊ

*ሕዝባዊ አመፆችም ሆኑ በጥሩ ስልትና አመራር የተካሄዱ የትጥቅ ትግሎች በነጠላም ሆነ በመደጋገፍ አምባገነን አገዛዞችን ለመገርሰስ ያስገኙት ውጤት በታሪክ የተመዘገበ ነው:: ኢሕአፓ የሚያካሂደው ትግል ሁለ ገብ ማለትም ሁለቱንም ያቀፈ መሆን አለበት ብሎ ገና ከጠዋቱ አቋም የወሰደው ሁለቱ የትግል ስልቶች ተደጋጋፊ እንጂ ተጻራሪ ባለመሆናቸው አመች ሁኔታዎችን እየመረመሩና እየገመገሙ ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል ከሚል እምነት በመነሳት ነው ::*

*ሕዝባዊ ትግል ሊሰምር የሚችለው÷ ሕዝባዊ ትግል ከፊቱ የተደቀኑትን ውጣ ውረዶችን ሁሉ ተቋቁሞ ግቡን ሊመታ የሚችለው በጠራ ራዕይና አቋም ላይ በተመሠረተ አደረጃጀት ከተመራ ብቻ ነው:: ከላይ እንደጠቀስነው ያልተደራጀ ሕዝባዊ ትግል የውኃ ላይ ኩበት ነው:: ለጥቂት ጊዜ ቢንሳፈፍም ፈራርሶ መስመጡ የማይቀር ነው:: ስለሆነም ከድርጅት አንጻር ያለፍንበትን ገምግሞ የወደፊቱን መቀየስ አግባብነት ይኖረዋል:: ተደራጅቶ በመታገል ላይ የነበሩትን ሁኔታዎች በግልጽ ገምግሞ ችግሮችንና ድክመቶችን እንዲሁም ጠንካራ ጎኖችን በነጠረ ሁኔታ ማውጣት ለሕዝባዊ ትግሉ ድል ዋስትና ይሰጣል:: ግምገማው ከፖለቲካ ድርጅቶች መጀመር አለበት:: ወያኔ በገሃድና በስውር የአደራጃቸውንና ያንቀሳቀሳቸውን የፖለቲካ ድርጅቶች ወደጎን ትተን ባለፉት ዓመታት በሀገራችን ህልውና አግኝተው በተቃዋሚነት ሲንቀሰቃሱ የቆዩ የፖለቲካ ድርጅቶች በርካታ መሆናቸውን እንረዳለን:: ወያኔን በመቃወም በኩል ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም በአንዳንዶቹ መካከል የነበረውና ያለው የዓላማ ልዩነት ትግላቸው ተደጋጋፊ ሆኖ ውጤት እንዳያመጣ እንቅፋት ሲሆን ቆይቷል:: የተወሰኑ ብሔረሰቦችን ነፃ ለማውጣት የሚታገሉትና ለኢትዮጵያ አንድነትና ለዴሞክራሲ ለመታገል የቆሙ የፖለቲካ ኃይሎች ተደጋጋፊና ተባባሪ ሊሆኑ አይችሉም:: የብሔር ድርጅቶች የሚያነሷቸው ተገቢ ጥያቄዎች መልስም ሆነ መፍትሔ ሊያገኙ የሚችሉት በኢትዮጵያ አንድነትና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሥር መሆኑን ሊገነዘቡ ይገባል:: ከኢትዮጵያ አንድነትና ከዴሞክራሲ ሁሉም ተጠቃሚ እንጂ ማንም ተጎጂ ሊሆን እንደማይችል ተረድተው አላማቸውን ቢያስተካክሉ በአምባገነን አገዛዝ ላይ የሚካሄደው ትግል ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል ጥርጥር ሊኖር አይችልም::*

*በዓላማ አንድነት ኖሯቸው ማለትም በኢትዮጵያ አንድነትና በዴሞክራሲ የሚያምኑ መሆናቸውን አሳውቀው ሲንቀሰቃሱ በነበሩ ድርጅቶችም መካከል በተጨባጭ ሁኔታው ላይ ያላቸው ግንዛቤና በትግሉ ላይ ያላቸው እምነት የተለያዩ ሆኖ በመቆየቱና በተለያየ መንገድም በመሄዳቸው ትግላቸው ተደጋጋፊና ተባባሪ ሳይሆን ቀርቷል:: ወያኔ አምባገነን ነው÷ ያለሕዝባዊ ትግል ማስወገድ አይቻልም የሚል ጥርት ያለ አቋም ይዘው ገና ከመጀመሪያው ሲታገሉ የነበሩ ድርጅቶች መኖራቸው ግልጽ ሲሆን እስከ ግንቦቱ ምርጫ ድረስ ወያኔን በፓርላማ ትግል በይስሙላ ምርጫ ከሥልጣን እናነሳዋለን የሚሉ ድርጅቶች በርካታ ነበሩ:: ለነገሩ በግንቦቱ ምርጫ ማግስት ከደረሰው የጅምላ ጭፈጨፋ በኋላ አሁንም በፓርላማ ትግል ወያኔን አሸንፈን እንጥላለን ብለው የሚፍጨረጨሩ መኖራቸው ግልጽ ነው:: ወያኔን ጠላት አድርጎ ፈርጆ በመታገልና በውስጡ ገብቶ ከውስጥ ቀስቅሶ ቀስ  በቀስ በመቀየር ለውጥ ማምጣት ይቻላል በሚለው ላይ የነበረውና ያለው የአመለካከት ልዩነት ወያኔን በሚቃወሙ የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ተደጋጋፊነትና ተባባሪነት እንዳይኖር ምክንያት ሲሆን ቆይቷል:: ብዙዎቹ የፖለቲካ ድርጅቶች ሀገራችንን ወደ እድገትና ወደ ዴሞክራሲ ሊያሸጋግሩ የሚችሉ መልካም መልካም ጉዳዮች በፕሮግራማቸው አስፍረዋል:: መታወቅ ያለበት ግን ፕሮግራማቸው ለሕዝብ ምርጫ ሊቀርብ የሚችለውና ሕዝብ ከደገፋቸው ሥልጣን ይዘው ፕሮግራማቸውን ተግባራዊ ሊያደርጉ የሚችሉት የወያኔ አምባገነነን አገዛዝ ሲገረሰስ ብቻ ነው:: ወያኔ በፈቃደኛነት ሥልጣኑን ለሕዝብ ሊያስረክብ ይችላል የሚለውን ቅዠት ወደጎን አድረገው ትኩረታቸውና አቅጣቸው ወያኔን በማስወገድ ላይ ቢሆን  ባጭር ጊዜ ውስጥ ውጤት ማስገኘት ይቻላል::*

*ሕዝባዊ ትግሉ ውጤት እንዲኖረው ለማድረግ የአገር ወዳድ ኢትዮጵያውንን ተደራጅቶ መታገልን ይጠይቃል:: በአሁኑ ወቅት በፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ ገብቶ ለትግሉ*

አስተዋጽኦ እያደረገ ያለው ዜጋ ኢትዮጵያዊ ቁጥር በጣም አነስተኛ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም:: ከመብት መረገጥ እንዲሁም ከበደልና ከስቃይ የተላቀቀ÷ ሰላምንና ብልጽግና የተላበሰ ኑሮ ለራሳችንና ለልጆቻችን ለማመቻቸት ፍላጎቱ ካለን÷ የሀገራችንን አንድነትና ልዕልና ለማስጠበቅ እምነቱና ዝግጁነቱ ካለን ተደራጅተን በመታገል አምባገነንነትን ማስወገድ ሀገራዊና ሕዝባዊ ግዴታችን መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል:: በዚህ በኩል የመጀመሪያው ኃላፊነት የሚወድቀው በፖለቲካ ድርጅቶች ላይ ነው:: በዓላማቸው ላይ ጥርት ያለ አቋም ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ዓላማቸውን ለሕዝብ ግልጽ አድርገው ታጋዩን አሳምነውና መልምለው ማታገል ሀገራዊ ግዴታቸው ነው:: ሶስትና አራት አባላትን ይዞ ድርጅት ነኝ ብሎ መመጻደቅም ሆነ የማይሆን ተስፋ ለሕዝብ እየሰጡ በተሳሳተ ጎዳና መጓዝ ለትግሉ ጉዳት እንጂ ጥቅም እንዳላመጣ ከተመክሯችን ተረድተናል:: ትግሉ ብዙ ውጣ ውረድ ያለበት መሆኑን ተረድተው÷ ትግሉ አምባገነን አገዛዝ ከማስወገድ በመለስ መቆም የማይኖርበት መሆኑን ተገንዝበው ጥርት ባለ አላማና ጉዞ ታጋዩን እያሰባሰቡ ማታገል ከሀቀኛ ድርጅቶች የሚጠበቅ ተግባር ነው:: በፖለቲካ ድርጅቶች አባልነት ያልተጠቃለለው አገር ወዳድ ደግሞ ካልተደራጁ መታገል÷ ካልታገሉ ድል ማድረግ የማይቻል መሆኑን ተረድቶ የፈለገውን ድርጅት ተቀላቅሎ ወይም የራሱን ድርጅት መስርቶ መታገል ሀገራዊ ግዴታው ነው:: ከየትኛው ድርጅት ገብቶ መታገል እንዳለበት ባለፉት አስራ ስምንት ዓመታት ያሳለፈው ተመክሮ ሊያስተምረው ይገባል:: የትኛው ድርጅት የጠራ አቋም አለው÷ የትኛው ቃሉን ጠብቋል÷ የትኛው ስህተቱን አርሞ በተገቢው መንገድ ተንቀሳቀሷል የሚለውን እየገመገመ መቀላቀል ይችላል::

በአገር ውስጥ የአምባገነኑ አገዛዝ የስለላና የማፈኛ ተቋሞች የተጠናከሩ በመሆናቸው ትግሉ በአብዛኛው መካሄድ ያለበት በህቡዕ በመሆኑ በሚፈለገው መጠን ተደራጅቶ ለመንቀሳቀስ ከበድ ያለ ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚችል ነው:: በህቡዕ እየተንቀሳቀሱ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ለመታገል የሚፈልጉትን ሀቀኛ ታጋዮች ለመመልመልም ሆነ አገር ወዳዶች ከሚፈልጉት ድርጅት ውስጥ ለመግባት መንገዱ ቀላል አለመሆኑ ግልጽ ነው:: ትግሉ እያደገና እየተጠናከረ ሲሄድ እነዚህ ችግሮች እየተወገዱ መሄዳቸው የማይቀር መሆኑ በተመክሯችን ያየነው ሐቅ ቢሆንም ያ ሁኔታ እስኪደርስ ጊዜ ግን አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በራሳቸው ተነሳስተው በተወሰነ ደረጃም እንኳ ቢሆን ተሰባስበው ራሳቸውን ለዋናው ትግል ሊያዘጋጁ ይገባል እንላለን:: ስለ ሀገር ጉዳይ መከታተል÷ ከሚያምኗቸው ወዳጆቻቸው ጋር መመካከር÷ ከዘመድ ከጓደኛ÷ ከሥራ ባልደረባ÷ ወዘተ...ጋር ሁለትም ሶስትም እየሆኑ በሀገር ጉዳይ እየተወያዩ ራስን ለትግል ማዘጋጀት ለሕዝባዊ ትግሉ አስተዋጽኦ ይኖረዋል:: የእቁብ÷ የእድር÷ የሙያና የመሳሰሉት ማኅበሮች ውስጥ ስለአገር ጉዳይ መወያየትና የሚበጀውን ማድረግ ትግሉን ለመርዳት መሠረት መጣል መሆኑ ሊታወቅ ይገባል:: በጥቂት በጥንቃቄ የተጀመረ ውጥን እያደር እያደገ ሄዶ በመጨረሻ የሚፈለገውን ውጤት ሊያመጣ እንደሚችል ጥርጥር ሊኖረው አይችልም::

ለአንዲት ቀን እንኳን ከትግሉ ሜዳ ያልተለየው ኢሕአፓ አስፈላጊውን መሥዋዕትነት እየከፈለ የወያኔን አምባገነን አገዛዝ እየተፋለመ ቆይቷል:: አሁንም እየተጋለ ነው:: በሀገራችን አምባገነንነት ተወግዶ÷ የሕዝብ መብት የተከበረበት÷ የሕግ የበላይነት እውን የሆነበት÷ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን እስኪሆን ድረስ ማናቸውንም መሥዋዕትነት እየከፈለ አምባገነን አገዛዝን ከመታገል ወደኋላ እንደማይል ለሕዝባችን በድጋሚ ቃል እየገባ የተደራጀ ሕዝባዊ ትግል ምን ጊዜም አቸናፊ መሆኑን ያለውን እምነት ይገልጻል:: ሕዝብም ከጎኑ ሆኖ ትግሉን እንዲያፋፍም ጥሪውን ይደግማል::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ድልን ይቀዳጃል!

እናቸንፋለን!!